የሰ/መ/ቁ፡- 240767

ጥቅምት 28 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

**አመልካች፡-** አቶ አለማየሁ ነጋሳ - ጠበቃ ካሳሁን አዲሱ - ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** ወ/ሮ ሸዋዬ አብዲሳ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የጋብቻ ፊች ውሳኔን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ወንበራ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ፣ አመልካች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 23 ቀን 2013 ዓ.ም ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ከተጠሪ ጋር በትዳር በቆዩባቸው 8(ስምት) ዓመታት የተፈሩ ናቸው ያሉትን ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሖነውን በወንበራ ወረዳ ደብረ

ዘይት ከተማ 02 ሳንቂ በር በሚባል አከባቢ የሚገኝ 58 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት እና 28 ዝንጎ ቆርቆሮ የተሰራ ማእድ ቤት እና ሌሎች በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ የጋራ ሀብት ናቸው የሚሉትን ንብረቶችን ጨምሮ የሚስትነት ድርሻቸው እንዲወሰንላቸ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ያቀረቡት የንብረት ዝርዝር አቤቱታ ከፍርድ ቤቱ መጥሪያ ጋር ድርሷቸው በሰጡት መልስ፡- ከተጠሪ ጋር ለ8 አመት በጋብቻ መቆየታቸውን ሳይክዱ ተጠሪ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ላይ የተመለከተው 58 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት በጋብቻ ውስጥ የተሰራ የጋራቸው ቢሆንም በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራው ማእድ ቤት ግን ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የገዙት የግላቸው በመሆኑ የጋራ ንብረት አለመሆኑን እና ሌሎች ንብረቶችን በተመለከተም ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የወንበራ የወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ስምቶ መዝገብን እንደመረመረው፡- ግራ ቀኙ በ2005 ዓ.ም ሲጋቡ 30 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት የአመልካች የግል ንብረት ተብሎ ከተመዘገቡት ንብረቶች መካከል መሆኑ በምስክሮች የተረጋገጠ ቢሆንም በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖርያ ቤት በአመልካች እና በተጠሪ በጋራ የተሰራ መሆኑ በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ አመልካች በጽሑፍ በሰጡት መልስ የታመነ በመሆኑ አመልካች ተጠሪን ከማግባታቸው በፊት የገዙትን 28 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤትን ጨምሮ 58 ዚንጎ ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት የጋራ ሀብት በመሆኑ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ያቀረቡት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በየደረጃው ባሉት ጉዳዩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማጣቱ ለሰበር አቤቱታ መቅረብ ምክንያት ሆኗል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል በሰበር ለማስለወጥ ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ በአጭሩ፡- አመልካች በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራው ቤት ከጋብቻ በፊት የገዛሁት የግሌ ለመሆኑ በጋብቻ ውል ጭምር መስፈሩ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን በተጠሪ በኩል ይህን በመቃወም የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሳይኖር የወንበራ ወረዳ ፍርድ ቤት በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት በጋብቻ ውስጥ ተሰርቷል በሚል ከጋብቻ በፊት የገዛሁትን በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ይካፈሉ በማለት መወሰኑ ፤ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎትም የወንበራ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናታቸው የክልሉን የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 78 ፤ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 26839 እና 53814 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔዎችን የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሻሽሎ በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራውን ቤት ከጋብቻ በፊት የተገዛ የአመልካች የግል ንብረት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠሪ በሰበር አቤቱታ ላይ የጽሑፍ ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪ ተደርጎላቸው መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ያላቀረቡ መሆኑ ስለተረጋገጠ በጽሑፍ መልስ የማቅረብ መብታቸው ታልፏል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

ባልና ሚስት ጋብቻ በምመሰርቱበት ጊዜ በግል የነበራቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግላቸው እንደሆነ የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ገሙዝ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 63/1998 አንቀጽ 78(1) ያመልክታል፡፡ ጋብቻ በተጋቢዎቹ ግላዊ ግንኙነት እና ንብረት በኩል ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ በፍቺ ውሳኔ ቀሪ ከሚሆኑት ውጪ ያለው ሕጋዊ ውጤት በተመለከተ በተጋቢዎች ስምምነት ወይንም በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚቋጭ ይሆናል፡፡ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ ጋብቻ ሲፈፀም ወይንም በፍቺ ወቅት የተደረገ የሚፀና ሕጋዊ ውል በማይኖርበት ጊዜ የባልና ሚስት ንብረት ተጣርቶ የግል የሆነውን ባለንብረቱ የሚወስድ ሲሆን ፤ የጋራ የሆነው ንብረት በሕጉ አግባብ ባልና ሚስቱ እንዲካፈሉ የሚወሰን መሆኑን የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 63/1998 አንቀጽ 106 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ በተጋቢዎቹ እጅ ያሉ ንብረቶች በማን ስም ተመዘገቡ የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ የጋራ ሀብት እንደሆኑ ስለሚቆጠር የግል ንብረቱ ነው የሚል ተጋቢ የግሉ/ሏ መሆኑን የማስረዳት ግዴታን እንዳለበት አንቀጽ 84(1) ያመለክታል፡፡ በጋብቻ ውስጥ በግል ሀብት ለውጥ የተገኘ ንብረት ወይንም በግል ገንዘብ የተገዛ ወይንም የግል ንብረቱን ሽጦ የሚያገኘው ገንዘብ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ይባልልኝ የሚል ጥያቄ ለፍርድ ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ ብቻ የግል ሀብት ሊሆን እንደሚችል አንቀጽ 79 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በጋብቻ ውስጥ በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሠራው ቤት ማዕድ ቤት የሖነው በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት የጋራ ሀብት ነው በማለት ተጠሪ ላቀረቡት አቤቱታ አመልካች በሰጡት መልስ በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሠራው ቤት በጋብቻ ውስጥ የተሰራ የጋራ ሀብት ቢሆንም በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤቱን ከጋብቻ በፊት የገዛሁት የግል ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በማስተባበል በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ ግራ ቀኙ ጋብቻ ሲመሰርቱ በ30 ዚንጎ የተሠራው ቆርቆሮ ቤት የተጠሪ የግል ሀብት መሆኑ በአመልካች ማስረጃ መረጋገጡን የወንበራ ወረዳ ፍርድ ከሰጠው ፍርድ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍርድ ቤቱም በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሠራው ቤት የጋራ ሀብት ነው በማለት የወሰነው ቤቱ በጋብቻ ውስጥ ስለተፈራ ወይንም የግል ቢሆንም በጋብቻ ውል የጋራ ስለሆነ ሳይሆን በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት በጋብቻ ውስጥ የተሠራው በመሆኑ ነው፡፡ የሰበር ሰሚው ችሎት የአንዱ ተጋቢ የግል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የነበረ ንብረት በጋብቻ ውስጥ ከጋራ ሀብት በመሠረታዊነት ከተለወጠ የጋራ እንደሚሆን በሰበር መዝገብ ቁጥር 94952(በቅጽ 17 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም በተያዘው ጉዳይ በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሠራው በአመልካች ከጋብቻ በፊት የተገዛው ቤት እና በጋብቻ ውስጥ በ58 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራው ቤት የተለያዩ ቤቶች ስለሆኑ አስገዳጅ ውሳኔው ለተያዘው ጉዳይ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ ስለሆነም በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሠራው አመልካች ከጋብቻ በፊት የገዙት የግላቸው የሆነውን ቤት የጋራ ነው በማለት ከተጠሪ ጋር እኩል እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሳኔ የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ገሙዝ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 63/1998 አንቀጽ 78(1) እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) ድንጋጌን የሚቃረን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 12314 ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ፣ የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 19431 ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ፤ እንዲሁም የወንበራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17020/13 ግንቦት 9 ቀን 2014 በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሻሽሏል፡፡**

2. በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ ከተሠራው ቤት ውጪ በሌሎች ንብረቶች ላይ የተላለፈው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. በ28 ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራውን ቤት ከጋብቻ በፊት የተገዛ የአመልካች የግል ንብረት ነው በማለት ወስነናል፡፡

4. .በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ላስከተለዉ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5. የዉሳኔ ትክክለኛ ቅጅ ለስር ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ይመለስ፡፡**

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !